በሎስ አንጀለስ የአንድነት/የቅንጅት የርዳታና ልማት ድርጅት ለዲሞክራሲ
Andinet/Kinijit’s Los Angeles Support and Development
Association for Democracy (KINIJIT)
5768 W. Pico Blvd., Suite No. 207, LA, CA 90019
email: kinijitla@kinijitla.org, website www.kinijitla.org

12/30/08

## *የሀገራችንን ብሩህና ጀግና ልጆች ለጅብ ማጋጋ እየሰጡ መቀመጥ ይቁም!*

*ለእውነት በመቆማቸው ለብሏት ያሰቧትን አሞራ ጅግራ ይሏታል እንዳሉ የተቀናቃኞቹን አፍ ለማዘጋት የኢህአዴግ መንግሥት ተብየው የወሸት ወንጀል በየጊዜው ከሚያመርትበት ፋብሪካ የፈጠራ ክስ በመመስረት የአንድነት ለዲሞክራሲና ፍትህ ሊቀ-መንበር ወይዘሪት ብርቱካን ሚዴቅሳን ወደቃሊቲ እስር ቤት አስገብተዋታል። በዚህ ተመሳሳይ የፈጠራ ክስ እስር ቤት የተወረወሩ የህሊና እስረኞች አያሌ ናቸው። የዕለት ከዕለት ሥራዬ ብሎ የተያያዘው ጉዳይ በመሆኑም ከአለፍትህ በዚህ መንገድ ወደእስር ቤት የሚወረወሩ ጀግኖች ወደፊትም ይኖራሉ።*

*በቆራጥ መሪዎቻችንና በኢትዮጵያ ብሩህ ልጆች ላይ ለከት የሌለው የአወሬ ተግባር ሊቆም የሚችለው ሁሉም ዜጋ በአንድነት ሸክሙ ከበደኝ ብሎ ሲነሳ እንደሆነ ስለምናምን እኛ የሎስ አንጀለስ የአንድነት ድጋፍ አካል ከመቼውም በበለጠ ለፍትህና ለዲሞክራሲ ከቆሙ ደርጅቶች ጋር በመተባበር ወ/ት ብርቱካን የታሰረችለት ዓላማ ግቡን እንዲመታ የትግል ፅናቷ ፅናታችን ሆኖ ትግላችንን እንቀጥላለን።*

*በወ/ት ብርቱካን ሚዴቅሳ ላይ የተወሰደው ኢፍትሃዊ እርምጃ ለዲሞክራሲ በሚታገሉት አያሌ ታጋዮች ላይ ከአለሚቋረጥ ሲካሄድ የነበረና ወደፊትም የሚቀጥል የጉልበተኛ ሥራ ስለሆነ ይህን አስከፊ የሆነ የዕብሪተኞች ተግባር በመተባበር እንድናስቆመው የሎስ አንጀለስ የአንድነት ድጋፍ አካል ጥሪውን ያስተላልፋል።*

*ወ/ት ብርቱካን ሚዴቅሳ፣ቴዎድሮስ ካሳሁንና ሌሎችም መሰል ወጣቶች ዛሬ የፈጠራ ክስ ተመስርቶባቸው በወያኔ ግፍ የሚፈጸምባቸው ለፍትህና ለዲሞክራሲ ስለታገሉ፤ ስለሀገር አንድነትና ፍቅር ስለዘመሩ ስለሆነ ለእውነት በመቆማቸው እየደረሰባቸው ያለው ስቃይ እኛንም እንደ ሾህ የሚወጋን ጉዳይ በመሆኑ ወጣት፣ሴት፣ ወንድና ሽማግሌ ሳንል ሁላችንም ትግሉን በመቀላቀል ለወድ ሀገራችን በጋራ ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ግዴታችንን እንደንወጣ በአንክሮት እናሳስባለን።*

*ዜጎችን የሚዋረደና ሀገር የሚጥፋት ተግባር ሊቆም የሚችለው ዕቅድ አወጥቶ ተግባራዊ ሥራ ሲሰራ በመሆኑ ከህዝቡ ጋር ተመካክሮ ሥራዎችን ለመሥራት በቅርብ በምናደርገው ጥሪ በመገኘት ዜጋዊ አስተዋፅዖን እንዲአደርጉ በዚሁ አጋጣሚ እናሳስባለን፡፡*

*የሎስ አንጀለስ የአንድነት ድጋፍ አካል*